## የድዳዋ የአስዳዳር የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር ............../፪ሺ፲፰

የትምባሆ ምርት የጤና፣የማህበራዊ፣የኢኮኖሚ እና አካባቢያዊ ችግር የሚያስከትሉ በመሆኑ፤ ትምባሆን መጠቀም እንደ ካንሰር፣ የመተንፈሻ አካል ህመም፣ የልብ እና የደም ስር የመሳሰሉትን በሽታዎች፣ የአካል ጉዳትን እንዲሁም ሞትን እንደሚያስከትል በሳይንስ የተረጋገጠ በመሆኑ፤

ለትምባሆ ጢስ መጋለጥ ትምባሆ በማያጨሱ ሰዎች ላይ ከፍተኛ የጤና ችግር፤ ሞት እና የአካል ጉዳት ስለሚያስከትል እና ይህንኑ መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሀገሪቱ ትምባሆን የሚጠቀሙ ወጣቶችና ጎልማሶች ቁጥር እንዳይጨምር፤ የትምባሆ ምርትን ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞት እና ስፖንሰር ማድርግ ትምባሆ የመጠቀም ፍላጎትን እንዲጨምር የሚያደርግ በመሆኑ እና ይህንን የትምባሆ ሽያጭ መንገድ መቆጣጠር አስፈላጊ እንደሆነ በመታመኑ፤

የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ በድሬደዋ አስተዳደር የምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፭ አንቀጽ (፸፯) ቤሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ
### ጠቃላይ ድንጋጌ

**፩፦ አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የድሬዳዋ አስተዳደር የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ ቁጥር ....../፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪፦ ትርጉሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

፩፦ **"አስተዳደር"** ማለት የድሬደዋ አስተዳደር ነው፤

፪፦ **"ባለስልጣን"** ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ነው፤

፫፦ **"አዋጅ"** ማለት የኢትዮጲያ የምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፲፪/፪ሺ፲፩ ነው፤

፬፦ **"ደንብ"** ማለት የድሬደዋ አስተዳደር የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፭ ነው፤

፭፦ **"የትምባሆ ምርት"** ማለት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከትምባሆ ቅጠል ተዘጋጅቶ በማጨስ፣ በመሳብ፣ በማኘክ፣ በማሽተት ወይም በሌላ መንገድ የሚወሰድ ማንኛውም ንጥረ ነገር ሆኖ የጋያ ወይም የሺሻ ትምባሆን ይጨምራል

## Dire Dawa Administration Health Bureau Tobacco Control Directive No. ……/2026

Whereas tobacco products cause health, social, economic and environmental problems; Whereas it is scientifically proven that tobacco use causes diseases such as cancer, respiratory diseases, cardiovascular diseases, physical disability and death;

Whereas exposure to tobacco smoke causes significant health problems, death and physical disability among non-smokers and it is necessary to control this;

Whereas the number of youth and adults using tobacco in the country does not increase; Whereas advertising, promotion and sponsorship of tobacco products increases the desire to use tobacco and it is necessary to control this way of selling tobacco;

The Dire Dawa Administrative Health Bureau has issued this directive in accordance with the authority granted by the Dire Dawa Administrative Food and Drug Administration Regulation No. 33/2015, Article 77

### Part One
### General

1. **Short Title**

   This directive may be cited as the *Tobacco Control* Directive *No. …/2026*

2. **Definitions**

   Unless the context otherwise requires, in this directive:

   1) "**Administration**" means the *Dire Dawa Administration*..
   2) "**Administrative Authority**" means the *Dire Dawa Administration Food, Medicine, and Health Care Authority*.
   3) . "**Proclamation**" means the *Ethiopian Food and Medicine Administration Proclamation No. 1112/2019*
   4) "**Regulation**" means the *Dire Dawa Administration Food and Medicine Administration Regulation No. 33/2022*
   5) "**Tobacco Product**" means any substance, partially or wholly prepared from tobacco leaves, intended for consumption by smoking, inhaling, chewing, sniffing, or by any other means, and includes shisha or cigarette tobacco.

| | |
|---|---|
| ፮፥ **ትምባሆ ምርት ማስተዋወቅ”** ማለት እንደ መገናኛ ብዙሃን፣ የውጭ ማስታወቂያን ፣ የቴሌኮምን፣ የፖስታ፣ የኢንተርኔት ድረ ገፅ እና የፋክስ አገልግሎቶችን እና መሰል የሆኑ መንገዶችን በቀጥታ በመጠቀም የትምባሆ ምርቶችን ወይም ትምባሆ መጠቀምን ለማበረታታት ተብሎ ወይም ሊያበረታታ በሚችል ሁኔታ የሚደረግ ማንኛውም አይነት የንግድ ግንኙነት፣ አስተያየት ወይም ተግባር ነው። | 6) “**Tobacco Product Promotion**” means any commercial activity, opinion, or action aimed at encouraging or likely to encourage the use of tobacco products or tobacco, directly through media, foreign advertising, telecommunications, postal services, internet websites, fax services, or similar means. |
| ፯፥ **“የትምባሆ ፕሮሞሽን”** ማለት የትምባሆ ምርትን በፅሁፍ፣ በድምጽ ወይም በምስል ከአንድ ፕሮግራም ጋር በማካተት፤ ለማህበራዊ ፋይዳ የሚውል መዋጮ ወይም ስጦታን በመጠቀም፣ የፕሮሞሽናል ቁሶች ወይም እቃዎችን በመስጠት እና መሰል በሆኑ መንገዶች በመጠቀም የትምባሆ ምርቶችን ወይም ትምባሆ መጠቀምን በተዘዋዋሪ ለማበረታታት ተብሎ ወይም ሊያበረታታ በሚችል ሁኔታ የሚደረግ ማንኛውም አይነት የንግድ ግንኙነት፣ አስተያየት ወይም ተግባር ነው። | 7) “**Tobacco Promotion**” means any commercial activity, opinion, or action aimed at indirectly encouraging or likely to encourage the use of tobacco products or tobacco, including incorporating tobacco products into written, audio, or visual programs, using social contributions or gifts, providing promotional items, or similar means. |
| ፰፥ **“የጤና ማስጠንቀቂያ”** ማለት ባለስልጣኑ በሚያስቀምጠው መስፈርት መሰረት በውጭ ማሸጊያ ላይ በጽሁፍ ወይም የባለቀለም ምስል ትምባሆ መጠቀም እና ለትምባሆ ጢስ መጋለጥ የሚያስከትለውን የጤና ጉዳት የሚያሳይ ማስጠንቀቂያ ነው። | 8) “**Health Warning**” means a warning, in writing or pictorial form, on the external packaging, as determined by the Authority, indicating the health risks associated with tobacco use and exposure to tobacco smoke. |
| ፱፥ **“ጅምላ ሻጭ”** ማለት የትምባሆ ምርትን ከአንድ ክልል በላይ በማከፋፈል ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ነው። | 9) “**Wholesaler**” means a person engaged in distributing tobacco products across more than one region. |
| ፲፥ **“የትምባሆ ቸርቻሪ”** ማለት የትምባሆ ምርቶችን ብቻ በመያዝ ትምባሆን በችርቻሮ የሚሸጥ ማንኛውም ሰው ነው። | 10) “**Tobacco Retailer**” means any person who sells tobacco products exclusively at retail. |
| ፲፩፥ **“ማጨስ”** ማለት የትምባሆ ጢስ በትንፋሽ ወደ ሰውነት ውስጥ እየተሳበ ወይም በትንፋሽ ወደ ውጭ የሚለቀቅ ሆኖ የተለኮሰ የትምባሆ ምርት የሚሞቅ የትምባሆ ምርት፣ የኤሌክትሮኒክ ኒኮቲን መስጫ መሣሪያ ወይም ከእነዚህ ጋር ተመሳሳይ ማንኛውም ምርት መያዝንም ይጨምራል። | 11) “**Smoking**” means tobacco smoke being inhaled into the body through breath or being exhaled out through breath; it also includes holding a heated tobacco product, an electronic nicotine or non-nicotinic delivery system, or any related product to these. |
| ፲፪፥ **“የህዝብ ማጓጓዣ”** ማለት ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ ወይም ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገርሰዎችን በክፍያ ለማጓጓዝ የሚያገለግል ማንኛዉም የመጓጓዣ አይነት ነዉ፡፡ | 12) “**Public Transport**” means any mode of transport used to carry people from one area to another or from one country to another for a fee. |
| ፲፫፥ **“አግባብ ያለው አካል**” ማለት እንደ አግባቡ በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱ ተግባራት በአስተዳደሩ ውስጥ በሚከናወንበት ጊዜ ድርሻ ያላቸውና በህግ ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት ናቸው ፡፡ | 13) “**Appropriate Authority**” means other entities with a role in the implementation of the functions specified in this regulation and authorized by law. |
| ፲፬፥ **“የፌዴራሉ ባለሰልጣን** ማለት የኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ነው | 14) **“Federal Authority**” means the Ethiopian Food and Medicine Authority. |

፲፭፥ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፮፥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

**፫፥ የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአስተዳደር ውስጥ በሚከናወኑ የትምባሆና ከትምባሆ ተያያዥ ምርቶች እና ከትምባሆ አጠቀቀም በተገናኘ ጉዳዮች ተፈፃሚ ይሆናል

## ክፍል ሁለት
## የልዩ ፈቃድ መስፈርቶች

**፬፥ ጠቅላላ**

፩፥ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሳያገኝ የትምባሆ ምርት ማከፋፈል አይችልም፡፡

፪፥ ከኢትዬጵያ የምግብ እና የመድሃኒት ባለስልጣን ልዩ ፈቃድ ባልተሰጠው የትምባሆ ምርትን ማምረት፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ ወይም በጅምላም ሆነ በችርቻሮ መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

፫፥ ማንኛውም የትምባሆ አብቃይ ወይም አምራች ሰው በትምባሆ ማብቀል ወይም ማምረት ምክንያት በሰራተኞቹ እና በአካባቢ ላይ የሚደረስን ጉዳት የመከላከልና የመቆጣጠር ግዴታ አለበት፡፡

፬፥ ከአዋጁና እና ሌሎች የማስፈጸሚያ ህጎች መሰረት የተከለከሉ ሺሻን ጨምሮ የትምባሆ ምርቶች፣ ማንኛዉም የትምባሆ ኒኮቲን ምርት ወይም ምርቱን መስጫ መሳሪያ ወይም ከሲጋራ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቴክኖሎጂ ማምረት፣ ማከፋፈል፣ ማጓጓዝ እና መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

፭፥ የአስተዳደሩ ጤና ቢሮ ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካል ጋር በመተባበር የትምባሆ አብቃይ አርሶ አደሮች ወደ ሌሎች የሰውን ጤና የማይጎዱ የምርት ዓይነቶች ማምረት እንዲገቡ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**፭፥ ስለ ልዩ ፈቃድ**

፩፥ ማንኛውም ሰው ከባለስልጣኑ ልዩ ፈቃድ ሳይሰጠው በአስተዳደሩ ውስጥ ለንግድ ተግባር የሚዉል የትምባሆ ምርት ማምረት፣ ማከፋፈል ፣ ወይም መቸርቸር አይችልም፡፡

፪፥ በትምባሆ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማራ ሰው በአስተዳደሩ ባለስልጣን ልዩ የቁጥጥር ፈቃድ የሚሰጠው የትምባሆ ምርትና ተያያዥ ጉዳዮችን ጥብቅ ቁጥጥር ለማድረግ እና የምርቱን ተጽኖውን ለመከላከል ዓላማ ይሆናል፡፡

**፮፥ የልዩ የቁጥጥር ፈቃድ መስፈርት**

፩፥ በትምባሆ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት ልዩ የቁጥጥር ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው

15) “**Person**” includes a natural person, and any entity granted legal personality.

16) Any reference to the male gender includes the female gender.

**3. Scope of Application**

This Directive shall apply to tobacco and tobacco-related products within the Administration, and to issues related to tobacco use

## Part Two
## Special Permit Requirements

**4. General**

1) No person may distribute tobacco products without obtaining a special permit from the administrative authority.

2) It is prohibited to produce, distribute, store, transport, or sell tobacco products, either wholesale or retail, without a special permit from the federal authority.

3) Any tobacco user or producer has the obligation to prevent and control the harm caused to employees and the environment due to tobacco cultivation or production.

4) In accordance with Proclamation No. 1112/2019 and other enforcement laws, the production, distribution, storage, transportation, or sale of tobacco products, including shisha, any nicotine-containing tobacco product, or any product or device used for smoking, or any technology similar to cigarettes, is prohibited.

5) The Health Bureau of the administration, in collaboration with other relevant bodies, will support tobacco-growing farmers to transition producing other types of products that do not harm human health.

**5. Regarding Special Permits**

1) No person may produce, distribute, or sell tobacco products for commercial purposes within the administration without obtaining a special permit from the administrative authority.

2) A special control permit issued by the administrative authority to a person engaged in the tobacco trade will aim to strictly control tobacco products and related matters and to mitigate the impact of the product.

**6. Special Permit Control Requirements**

ስለተቋሙ ህጋዊነት ማረጋገጫ ማቅረብ፣ ሥራው ለማከናወን የሚጠየቅን መስፈርት የሚያሟላ ቦታ ያለው፣የአገልግሎት ክፍያ መክፈል እና ተያያዥ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፡፡

፪፦ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 መሰረት ልዩ የቁጥጥር ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም አምራች ወይም አከፋፋይ ማከማቻን ጨምሮ ልዩ ፈቃድ ከተሰጠበት ቦታ እና የሥራ ዓይነት ውጭ ለማከናወን አይችልም፤ የአድራሻ ወይም የምርቱን የስራ ዓይነት ለውጥ ለማድረግ ወይም ለመጨመር በቅድሚያ ለባለስልጣኑ ማሳወቅና ማስፈቀድ አለበት፡፡

፫፦ በትምባሆ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት ልዩ የቁጥጥር ፈቃድ የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው በተቋሙ ላይ የትምባሆ ምርት ንግድ ስራ የሚሰራ መሆኑን የሚያሳይ ማንኛዉንም አይነት የምርቱን ስም፣ሎጎ የያዘ ማስታወቂያ ሰሌዳ በተቋሙ በሚታይ የዉጭ ክፍል ላይ መለጠፍ የለበትም፡፡ ከትምባሆ ምርት ውጭ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ኒኮቲንን በመጠቀም ለሰው ፍጆታነት የሚውል ማንኛውንም ዓይነት ምርት አስተዳደሩ ውስጥ ማምረት፣ማከፋፈል፣ ማከማቸት ወይም መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

፬፦ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (4) በሱስ ውስጥ ያለን ሰው ከሱስ ለማውጣት አገልግሎት ላይ የሚውል የኒኮቲን ሪፕለስመንት ቴራፒ ምርት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤በዚህ አግባብ ያለ ምርት መድኃኒት አስተዳደር የሚመራ ይሆናል፡፡

**፯፦ ለቸርቻሪ ስለሚሰጥ ልዩ ፈቃድ መስፈርት**

በዚህ መመሪያ አንቀጽ ፭ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የትምባሆ ምርት ለመቸርቸር ልዩ ፈቃድ ከባለሥልጣኑ መዉሰድ የሚፈልግ ቸርቻሪ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

፩፦ የችርቻሮ መደብሩ በደንቡ አንቀጽ ፴፱ ንኡስ አንቀጽ (፫) መሰረት ትምባሆ እንዳይሸጥ የተከለከለባቸዉ ቦታዎች የማይገኝ መሆኑን ማረጋገጥ፤

፪፦ የችርቻሮ ድርጅቱ ባለቤት በዚህ መመሪያ በተያያዘዉ አባሪ (፩) ላይ የተዘረዘሩ መስፍርቶችን ማሟላቱን በማረጋገጥ መፈረም፤

፫፦ በአገልግሎት ክፍያ ደንብ የሚወሰነዉን ክፍያ መክፈል፡፡

**፰፦ ልዩ ፈቃድን ስለማደስ እና ለውጥ**

፩፦ ልዩ የቁጥጥር ፈቃዱ ሳይታደሰ ትምባሆ ማምረት፣ማከፋፈል፣ በችርቻሮ መሸጥ፣ ማከማቸት፣ ማጓጓዝ፣ ወይም ለገበያ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

1) Any person seeking a special control permit to engage in the tobacco trade must provide proof of the legality of the institution, have a suitable location to carry out the work, pay the required service fee, and meet other related requirements.
2) Any producer or distributor who has been granted a special control permit under Article 4 of this directive may not operate outside the location and type of work specified in the permit. Any change or addition to the address or type of product must be notified and approved in advance by the administrative authority.
3) Any person seeking a special control permit to engage in the tobacco trade must not display any type of advertisement, including the product name or logo, on the external part of the institution. The production, distribution, storage, or sale of any product containing natural or artificial nicotine for human consumption within the administration is prohibited.
4) Sub-article (4) of this article does not apply to nicotine replacement therapy products used for smoking cessation services. Such products will be regulated by the Drug Administration.

**7. Requirements for Retail Special Permits**

In addition to the requirements set out in Article 5 of this directive, any retailer seeking a special permit to sell tobacco products must meet the following requirements:

1) Ensure that the retail shop is not located in areas where tobacco sales are prohibited under Article 39, Sub-article 3 of the regulation.
2) Confirm that the owner of the retail business meets the requirements listed in Appendix 1 of this directive and sign accordingly.
3) Pay the fee determined by the service fee regulation.

**8. Renewal and Amendment of Special Permits**

1) It is prohibited to produce, distribute, sell, store, transport, or market tobacco products without renewing the special control permit.

፪፦ በዚህ መመሪያ በአንቀፅ ፭ መሰረት የተሰጠ ልዩ ፈቃድ የሚፀናው ለአንድ የመንግስት በጀት ዓመት አመት ሆኖ ፈቃዱ ከበጀት ዓመቱ ጀምሮ ላይ መታደስ አለበት፡፡

፫፦ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሰረት ልዩ የቁጥጥር ፈቃድ የሚታደሰው የመንግስት በጀት ዓመት በገባ ስድስት ወር ውስጥ ባለው ጊዜ ይሆናል፡፡

፬፦ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) መሰረት ልዩ የቁጥጥር ፈቃዱን ያላሳደሰ ሰው በመመሪያ በሚወሰን ቅጣት በቀሪዎቹ ፮ ወር ለማሳደስ ይችላል፡፡ በአንድ ዓመት ጊዜ ዉስጥ ያላሳዳሰ ከሆነ ልዩ ፈቃዱ እንደተሰረዘ ይቆጠራል፡፡

፭፦ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) እና (፬) መሰረት በቅጣት ማሳደስ ያልቻለ ሰው በቅጣት ማሳደሻ ማብቂያ ጊዜ ጀምሮ ለሚታሰብ ለአንድ ዓመት በስራው ላይ ለመሰማራት እንዲሁም አዲስ ልዩ የቁጥጥር ፈቃድ ማውጣት አይችልም፡፡

**፱፦ ትምባሆ ምርት ጤና ማስጠንቀቂያና ገላጭ ጽሑፍ**

፩፦ ማንኛውም በአስተዳደሩ የሚመረት፣የሚከፋፈል ወይም የሚሸጥ የትምባሆ ምርት ገላጭ ጽሑፍ የሚይዘው የድርጅቱን ስምና ዓርማ፣ የንግድ ስምና ምልክት፣ ባር ኮድ፣ የታክስ ቴምብር እና በህግ እንዲኖረው የሚጠየቅ መረጃን ብቻ ይሆናል፡

፪፦ የትምባሆ ምርት ማሸጊያ፣ የድርጅቱ ስምና ዓርማ፣ የብራንድ ስምና ስዕል የቀለም ሁኔታ ተግባራዊ የሚደረግን የጤና ማስጠንቀቂያ የሚያውክ ወይም የጎላ ሆኖ የጤና ማስጠንቀቂያውን የሚያደበዝዝ ወይም ጎልቶ እንዳይታይ የሚያደርግ መሆን የለበትም፡፡

፫፦ የትምባሆ ምርት የጤና ማስጠንቀቂያ ባለቀለም ምስልና መልዕክት በምርቱ ተቀዳሚ ማሸጊያ ላይ የታተመና የሚታይ መሆን አለበት፡፡

፬፦ በአዋጅ ተግባራዊ እንዲደረግ የተሰጠን የጤና መስጠንቀቂያ መቀየር፣ እንዲደበዝዝ ማድረግ፣ በቅርጽም ሆነ በይዘት ለውጥ ማድረግ ወይም በሌላ ማንኛውም መንገድ ከተሰጠበት ሁኔታ መቀየር ወይም በተቀዳሚ ማሸጊያው ላይ በስቲከር ወይም በሌላ መንገድ መለጠፍ የተከለከለ ነው፡፡

፭፦ የጤና ማስጠንቀቂያዉ ሌሎች አስፈላጊበሆኑ የማሸጊያ ወይምገላጭ ጽሁፍ መስፈርቶች ወይም አምራቹ፣ አስመጪው፣ ጅምላ አከፋፋይ ወይም ሌላ ማንኛውም የትምባሆ ነጋዴ በማሸጊያው ላይ በሚያስቀምጠው ሌላ ማንኛውም ነገር መሸፈን ወይም መከለል የለበትም፡፡

2) A special permit issued pursuant to Article 5 of this directive shall be valid for one government fiscal year and shall be renewed starting from the beginning of each fiscal year.

3) The special permit issued pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be renewed within six months from the beginning of the government fiscal year

4) A person who fails to renew his special permit pursuant to sub-article (2) of this article may, subject to a penalty determined by regulation, renew it for the remaining six months. If he fails to renew it within one year, his special permit shall be deemed to have been revoked.

5) A person who has failed to serve a sentence pursuant to sub-articles (3) and (4) of this article shall not be permitted to engage in any work or to issue a new special control permit for a period of one year from the date of expiration of the sentence

**9. Health Warnings and Labeling on Tobacco Products**

1) Any tobacco product produced, distributed, or sold within the administration must include labeling that contains only the company name and logo, trade name and mark, barcode, tax stamp, and other information required by law.

2) The packaging of tobacco products must not obscure or diminish the visibility of the health warning, nor should the company name, logo, brand name, or design interfere with the health warning.

3) The health warning on tobacco products must be printed on the primary packaging and must be visible.

4) It is prohibited to alter, obscure, or change the health warning in any way, including adding stickers or other materials to the primary packaging.

5) The health warning must not be covered or obscured by any other necessary packaging or labeling information, or by anything else placed on the packaging by the manufacturer, supplier, wholesaler, or any other tobacco trader.

፮፥ የጤና ማስጠንቀቂያ ጽሁፍ በአማርኛ ወይም በእንግዘኛ ቋንቋ መጻፍ አለበት፡፡

**፲. ስለትምባሆ ምርት መረጃ እና ይዘቶች**

፩፥ በኢትዮጵያ የምግብ እና መድሃኒት ባለሥልጣን የተከለከለ ይዘት ያለበትን የትምባሆ ምርት ጅምላ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ የተከለከለ ነው፡፡

፪፥ የዚህ አንቀጽ ንኡስ-አንቀጽ (1) እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ማሸጊያው ወይም ገላጭ ጽሁፉ ተጨማሪ ጣዕም እንዳለው ቢያመላክትም ባያመላክትም ልዩ ጣዕም ያለው፤

ለ) በምርቱ ክፍል ውስጥ ወይም በምርቱ ማሸጊያ፣ መጠቅለያ እና ሌላ ከምርቱ ጋር ንክኪነት ባለው ነገር ላይ የትምባሆን ሽታ ወይም ጣእም የሚቀይር ማጣፈጫ የያዘ፤

ሐ) የትምባሆ ምርት ይዘቶች ለጤና የሚጠቅም ወይም ጤና ላይ የሚያስከትልን ጉዳት የሚቀንስ የሚያስመስሉ እንደ ቫይታሚን፣ ፍራፍሬ እና አትክልቶች፣ አሚኖ አሲድ፣ ካፊን፣ ቶሪን ወይም መሰል አነቃቂ ንጥረ ነገር፣ ጠቃሚ ፋቲ አሲዶች ወይም ሀይልን እና ጥንካሬን ከመስጠት ጋር የተያያዙ አነቃቂ ሌላ ውህድ የያዘ ወይም ከነዚህ ባህሪዎች ጋር በተመሳሳይ መልኩ ሊገናኝ የሚችል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጭማሪ የያዘ፤

መ) የትምባሆ ጪስን የሚቀይር ማቅለሚያ የያዘ፤ የትምባሆ ምርትን ማምረት፣ በጅምላ መሸጥ፣ ማከፋፈል፣ ወይም በችርቻሮ መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

**፲፩. ትምባሆ ማጨስ እና መጠቀም ስለሚከለከልበት ቦታ**

፩፥ ማንኛውም ሰው ከበር መልስ ባለ ለህዝብ ክፍት በሆነ ማንኛውም ቦታ፣ ከበር መልስ ባለ ማንኛውም የስራ ቦታ፣ በሁሉም የህዝብ መጓጓዣ እና በጋራ መኖሪያ ቤት ማንኛውም የጋራ መገልገያ ቦታ ላይ ትምባሆን ማጨስ ወይም መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

፪፥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሰረት ማጨስ ወይም ትምባሆን መጠቀም በተከለከለባቸው ከበር መልስ ባሉ ለህዝብ ክፍት በሆኑ ቦታዎች እና የስራ ቦታዎች በአስር ሜትር ዙሪያ ውስጥ ባለ መግቢያ በር፣ መስኮት ወይም አየር ወደ ውስጥ ሊያስገባ በሚችል ሌላ ቦታ ውስጥ ማጨስ የተከለከለ ነው፡፡

፫፥ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) ቢኖርም በማንኛውም የጤና ተቋም፣ የመንግስት ተቋም፣ ለህጻናት ማቆያ፣ መናሃሪያ፣ ትምህርት ቤትን፣ የትምህርት ወይም የስለልጠና ተቋማትን፤ የምግብ ወይም የመጠጥ ወይም የመኝታ አገልግሎት ሰጭ ተቋም፣ ወጣት ማዕከል፣ ሆቴልና የሆቴል ክፍሎች፣ ሬስቶራንት፣ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የገበያ ማእከል፣ ባዛር፣መዝናኛ ፓርክ ከበር መልስ ጨምሮ በቅጥር ጊቢ ውስጥ ማጨስ ወይም ትምባሆ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

6) The health warning text must be written in Amharic or English.

**10. Information and Contents of Tobacco Products**

1) It is prohibited to distribute, sell, or offer for sale any tobacco product containing substances banned by the federal authority.

2) In accordance with Sub-article (1) of this article, no person may:

a) Indicate or imply that the product has a special flavor, whether or not the packaging or labeling suggests additional flavor.

b) Include any additive that alters the smell or taste of tobacco in the product, its packaging, or any related material.

c) Include any substance that suggests health benefits or reduces health risks, such as vitamins, fruits, vegetables, amino acids, caffeine, taurine, or other stimulants, or any other ingredient that may be associated with providing energy or strength.

d) Include any additive that alters the color of tobacco ash. The production, wholesale distribution, or retail sale of such tobacco products is prohibited.

**11. Prohibition of Smoking and Use of Tobacco Areas**

1) Smoking or using tobacco is prohibited in any enclosed public place, any enclosed workplace, all public transportation, and any common area of shared residential buildings.

2) Smoking is also prohibited within ten meters of entrances, windows, or any other openings of enclosed public places and workplaces where smoking is banned under sub-article (1).

3) Despite sub-article (2), smoking or using tobacco is prohibited in the **entire premises, including buildings, compounds, and adjacent outdoor areas** of health institutions, government institutions, childcare centers, orphanages, schools, educational or training institutions, food or beverage service establishments, youth centers, hotels, hotel rooms, restaurants, industrial parks, market centers, bazaars, and amusement parks.

፬፦ ማንኛውም ሰው ትምባሆ ማጨስ ወይም መጠቀም በተከለከለባቸው ስፍራዎች፣ ተቋማትና አገልግሎት መስጫ ለትምባሆ ማጨሻ ወይም መጠቀሚያ ቦታ ማዘጋጀት የተከለከለ ነው።

፭፦ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም፦

ሀ) "ለህዝብ ክፍት የሆኑ ቦታ" ማለት ለማንኛውም ሰው ክፍት የሆነ ወይም ማንኛውም ሰው ሊጠቀምበት ወይም ሊገባበት የሚችል የጋራ መጠቀሚያ ማንኛውም ስፍራ ነው፤

ለ) "የስራ ቦታ" ማለት በክፍያም ይሁን ካለ ክፍያ ሰዎች የስራ ሀላፊነታቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የሚጠቀሙበት የጋራ ስፍራ ነው፤

ሐ) "ከበር መልስ ያለ ቦታ" ማለት የተሰራበት ቁሳቁስ አይነት እና መዋቅሩ ቋሚ መሆኑ ሳይወስነው ማንኛውም በጣሪያ የተሸፈነ እና አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆነ ግድግዳ የተከለለ ስፍራ ነው።

## ፲፪. የማስከበር ግዴታ

፩፦ ለህዝብ ክፍት የሆነቦታ ወይም መጓጓዣ ባለንብረት ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ሰው ወይም የስራ ቦታን በተመለከተ አሰሪ ወይም ሌላ ሀላፊነት ያለበት ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርት በማይጨስበት ቦታ ላይ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የማስከበር እና እንዳይጣስ የመጠበቅ ሀላፊነት አለበት።

፪፦ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ () መሰረት የሚከተሉትን ጨምሮ ሌሎች  አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ አለበት

ሀ) በጉልህ የሚታይ ማጨስ በህግ የተከለከለ ነው የሚል ማሳሰቢያ ከነምልክቱ በአማርኛ እና/ወይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ወይም በአካባቢው የስራ ቋንቋ እና በአማርኛ መለጠፍ አለበት።

ለ) ለማጨስ አጋዥ የሲጃራ  መተርኮሻ የሆኑ እንደነ አሽትሬ፣ መተርኮሻ ሌሎች መሳሪያዎችን እንዳይቀመጥ ማድረግ፣

ሐ) ለሰራተኞቻቸዉ የደንቡን እና የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ማድረግ።

መ) በተከለከሉ ቦታዎች የትምባሆ ምርት እንዳይጨስ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል፣ እንዳይሸጥ እና የሲጃራ መተርኮሻ ወይም ሌላ የትምባሆ ምርትን ለመጠቀም የሚያገለግል ማንኛውም እቃ እንዳይቀመጥ መከልከል አለበት።

ሠ) በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፊደል (ሐ) ድንጋጌ መሰረት ለማስቆም ሲሞክር ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው ቢኖር፣ ኃላፊነት ያለበት ሰው ቦታ ላይ ማጨስ በህግ የተከለከለና ተቋሙም ሆነ ተጠቃሚው በህግ እንደሚጠየቅ በመግለጽ አገልግሎቱን ማቋረጥና ቦታውን ለቆ እንዲወጣ ማድረግ አለበት።

ረ) የማስቆም ኃላፊነት ያለበት ሰው በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፊደል(ሠ) ድንጋጌ መሰረት አገልግሎቱን አቋርጦ እና ቦታውን ለቆ እንዲሄድ ጠይቆ ተጠቃሚው ፈቃደኛ ያልሆነለት እንደሆነ ለባለስልጣኑ፣ ለደንብ አስከባሪ ወይም ለፖሊስ ማሳወቅ አለበት፤ እነዚህ አካላት መረጃው ሲደርሳቸው ተጠቃሚውን በኃይል ማስወጣትን ጀምሮበህግ አግባብ እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

ሰ) በተቋሙ፣ በማጓጓዣው ወይም በአገልግሎት መስጫ የትምባሆ ማስታወቂያ ወይም ፕሮሞሽን እንዳይከናወን መከላከልና እና ሊሆኑ የሚችሉ ማናቸውም ጉዳዮችን ማስወገድ አለበት፤

4) No person shall prepare a smoking or tobacco-use area in places, institutions, or service areas where smoking or tobacco use is prohibited.

5) For the implementation of this article:

a) "Public place" refers to any place open to or accessible by the public;

b) "Workplace" refers to any common area where people perform their duties, whether paid or unpaid;

c) "Enclosed place" refers to any space covered by a roof and enclosed by one or more walls, regardless of the material used.

## 12. Enforcement Obligations of Smoke Free Areas

1) For the effective enforcement of smoke-free provisions, owners or responsible persons of public places, transportation, or workplaces must ensure compliance with this directive to prevent smoking or tobacco use.

2) The following measures must be taken:

a) Display clear signs in Amharic and/or English or the local working language stating that smoking is prohibited by law;

b) Ensure that ashtrays or other smoking accessories are not placed;

c) Educate employees about the regulations and this directive;

d) Prevent the sale, use, or placement of tobacco products or accessories in prohibited areas;

e) If a person refuses to comply, the responsible person must stop the service and ask the person to leave, informing them of the legal consequences;

f) If the person refuses to leave, the responsible person must notify the relevant authority, who will take legal action, including forced removal;

g) Prevent tobacco advertisements or promotions in the institution, transportation, or service areas;

ሸ) የባለስልጣኑ የቁጥጥር ባለሙያ የዚህን አንቀጽ አፈጻጸም ተግባራዊ መሆኑን በመከታተል ሂደት የትምባሆ ቁሩ፣ ተረፈ ምርት፣ የትምባሆ ሽታ እና ማስታወቂያ ሊሆኑ ከሚችሉ ነገሮች ቦታው ነጻ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

### ፲፫. ስለ ትምባሆ ምርት ሽያጭ

፩፥ ማንኛዉም አምራች ወይም አከፋፋይ ምርቱን መሸጥ የሚችለዉ ልዩ ፈቃድ ለተሰጠዉ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ይሆናል፡፡

፪፥ ማንኛዉም ቸርቻሪ ዕድሜው ፳፩ ዓመት ላልሞላው ሰው መሸጥ እና እንዲሸጥ ማድረግ የተከለከለ ነዉ፡፡ ይህ ክልከላ ተግባራዊ የሚሆነው የገዢውን ወይም የሻጭን ዕድሜ በአካላዊ ሁኔታ ወይም በመታወቂያ በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

፫፥ በንኡስ አንቀጽ (፪) መሰረት በአካላዊ ሁኔታ በማያጠራጥር ሁኔታ ዕድሜውን ለመለየት አስቸጋሪ ከሆነ፤ ዕድሜው መታወቂያውን ወይም ፓስፖርት፣ ወይም ማንኛዉም እድሜን ለማሳየት የሚችል ህጋዊ ሰነድ በማየት መረጋገጥ አለበት

፬፥ የትምባሆ ምርቶችን በድረ-ገጽ መሸጥን ጨምሮ የትንባሆ ምርትን ለመሸጥ ወይም እንዲሸጥ ለማድረግ ወይም ሽያጩን ለማቀላጠፍ ገዢ እና ሻጭ በአንድ ተመሳሳይ ቦታ ፊት ለፊት ሳይገናኙ የሚደረግ የትንባሆ መገበያ መንገድ መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

፭፥ ማንኛውንም ዓይነት የትምባሆ ምርት ለማስጨስ ወይም ለማስጠቀም የሚዘጋጅ የንግድ ስራ የተከለከለ ነው፡፡

### ፲፬. የባህላዊ ትምባሆ ምርቶች

ስለ ትምባሆ ምርት ሽያጭ፣ ማጨስ እና የመጠቀሚያ ቦታ በአዋጅ፣ ደንብ እና በዚህ መመሪያ የተደነገጉት ክልከላዎች በአስተዳደሩ ዉስጥ የሚቀርብ ማንኛዉም በባህላዊ መንገድ የሚዘጋጅ የትምባሆ ምርት ላይ በተመሳሳይ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

### ፲፭. ሲጋራን በነጠላ ስለ መሸጥ

፩፥ የሲጋራ ምርትን በነጠላ መሸጥ የተከለከለ ነው፡፡

፪፥ ማንኛውም ሲጋራ የሚሸጠው ሃያ ሲጋራዎችን በያዘ ባልተከፈተ ፓኬት ወይም በፌደራል አስፈጻሚ አካሉ በሚወሰን የትምባሆ ቁጥር ወይም ክብደት መሰረት ነው፡፡

፫፥ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ነጠላ" ማለት በሲጋራ ፓኬት ውስጥ ከሚገኙ ሲጋራዎች ውስጥ በቁጥር አንዷን የሚገልጽ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ትምባሆን ማስተዋወቅ፣ፕሮሞሽን እና ስፖንሰር ማድረግ

### ፲፮. አጠቃላይ ክልከላ

፩፥ የትምባሆ ምርትን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ማስተዋወቅ፣ፕሮሞት እና ስፖንሰር ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

፪፥ የትምባሆ ምርት በተመለከተ ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞት እና ስፖንሰር ማድረግ ፍፁም የተከለከለመሆኑበዚህ ክፍልየተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ከዚህ ቀጥሎ

h) Ensure the area is free from tobacco residue, smell, or advertisements.

### 13. Regarding the Sale of Tobacco Products

1) Any manufacturer or distributor may sell products only to licensed distributors or retailers.
2) It is prohibited for any retailer to sell or facilitate the sale of tobacco to anyone under 21 years of age. This restriction is enforced by verifying the buyer's or seller's age physically or through identification.
3) If age cannot be determined physically without doubt, identification such as an ID card, passport, or any legal document proving age must be checked.
4) Selling tobacco products online or through any method where the buyer and seller do not meet face-to-face is prohibited.
5) Preparing any commercial activity for smoking or using tobacco products is prohibited.

### 14. Traditional Tobacco Products

The prohibitions on the sale, smoking, and use of tobacco products under the law, regulations, and this directive also apply to traditional tobacco products prepared in a customary manner.

### 15. Selling Cigarettes Individually

1) Selling individual cigarettes is prohibited.
2) Cigarettes must be sold in unopened packages containing at least 20 cigarettes, as determined by the federal executive body based on tobacco quantity or weight.
3) For this article, "individual" refers to a single cigarette from a package.

## Part Three:
## Introduction, Promotion, and Sponsorship of Tobacco Products

### 16. General Prohibition

1) It is prohibited to introduce, promote, or sponsor tobacco products, either directly or indirectly.
2) The absolute prohibition of introducing, promoting, or sponsoring tobacco products, as stipulated in this section, is to be strictly observed. The following actions, among others, are prohibited:

የተዘረዘሩት እና ሌሎች ተመሳሳይ ድርጊቶችን መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

ሀ) በድምፅ፣ በምስል ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል የግንኙነት መንገዶች፣ በህትመት፣ በፊልሞች፣ በቪዲዮ እና በሲዲ መጫወቻዎች ወይም ሌሎች የዲጅታል መገናኛዎች፣ቲያትር ወይም የቀጥታ ስርጭቶች አማካኝነት ወይም የምርት አማባሳደር በመሾም ማስተዋወቅ፣ ትምባሆን የሚመለከት ኮሚኒኬሽን ማድረግ፤

ለ) በበይነ መረብ መገናኛ ብዙሃን፣ በማህበራዊ የትስስር ገጾች፣ በድረ-ገጽ፣ በብሮድካስት፣ እና መሰል የዲጅታል ዘዴዎች ማስተዋወቅ፤

ሐ) የትምባሆ ምርቶቹን ለመሸጥ የሚደረጉ ስጦታዎች እና ትምባሆን ሲሸጡ እንደ ቁልፍ መያዣ፣ ቲሸርቶች፣ ኮፍያዎች እና የሲጋራ መለኮሻዎች የመሰሉ እቃዎች መስጠት ወይም በማንኛውም መንገድ መሰል ማበረታቻ ማድረግ፤

መ) የገበያ ጥናት እና የጣዕም ቅምሻን ጨምሮ መሰል ነገሮች በማድረግ የትምባሆ ምርቶችን ነፃ ናሙና ማቅረብ፤

ሠ) የዋጋ ቅናሽ መልእክትን ያዘለ በማንኛውም መንገድ የሚደረግ ማስተዋወቅ፣

ረ) የማበረታቻ ፕሮሞሽን እና የትምባሆ ምርቶችን ግዢ ለሚፈጽም ማንኛውም ሰው ሌሎች እቃዎችን የሚገዛበትን ነፃ ኩፖን መስጠትን ጨምሮ ሌሎች ተመሳሳይ የምርቃት (loyality schemes) አይነት ተግባሮችን መፈፀም፤

ሰ) የትምባሆ ምርት የብራንድ ስም፣ አርማ፣ የንግድ ምልክት፣ የድርጅት አርማ፣ የንግድ መለያ ወይም ሌላ ተመሳሳይ መለያን የትምባሆ ምርት ካልሆኑ ሌሎች ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ጋር ማያያዝ (brand stretching) ወይም ትምባሆ ነክ ያልሆኑ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን በተመሳሳይ መንገድ ከትምባሆ ምርት ጋር ቁርኝነት ወይም ተያያዥነት እንዳላቸው (brand sharing) ማሳየት፤

ሸ) መረጃን ጨምሮ ቀጥታ ግለሰቦች ላይ በማነጣጠር ቀጥታ መልዕክት ወይም ደብዳቤ መላክ፣ በስልክ መገበያየት፣የሸማቾች ቅኝት ወይም ጥናት ማካሄድን እና ተመሳሳይ አይነት የፕሮሞሽን መንገዶች መጠቀም፤

ቀ) የትምባሆ ምርት ነጋዴ የተወሰነ የትምባሆ መጠን ያለውን ምርት ሲሸጥ ሽልማት መስጠትን ጨምሮሌሎች የማበረታቻ ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም ሽያጭን ማበረታታት ጨምሮ ለትምባሆ ሻጭ የሚደረግ ተያያዥ ክፍያ ወይም ሌላ አይነት ድጋፍ ማድረግ፤

በ) በትምህርት ተቋማት፣ የጤና ተቋማት፣ የመስተንግዶ (hospitality) ቦታዎች፣ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች፣ በመዝናኛ ቦታዎች፤ በሙዚቃ እና ዳንስ ቤቶችእና የማህበራዊ ቦታዎች ወይም ዝግጅቶች ላይ የትምባሆ ምርቶችን መሸጥ፣ማቅረብ፣ ማስቀመጥ እና በግልፅ ማሳየት፤ እና

ተ)የትምባሆምርትን አሻንጉሊቶችን፣ ጣፍጭ ምርቶችን ወይም ሌሎች ምርቶችንበማስመሰል መሸጥ ወይም ማቅረብ፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፯. አስተዳደራዊ እርምጃ

፩÷ በዚህ መመሪያ የተቀመጠ ግዴታ፣ ኃላፊነት ወይም መስፈርት በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ሰው ላይ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

a) Using voice, images, or moving images through communication channels, print media, films, videos, CDs, or other digital media, theater, or live broadcasts, or by employing product placement to introduce or communicate about tobacco products.

b) Introducing tobacco products through internet media, social networking sites, websites, broadcasts, or similar digital methods.

c) Offering gifts or incentives such as keychains, T-shirts, caps, cigarette lighters, or similar items when selling tobacco products, or providing any form of promotional incentive.

d) Conducting market research or taste tests, including offering free samples of tobacco products.

e) Introducing any form of promotion that includes price reduction messages.

f) Implementing loyalty schemes, including providing free coupons for purchasing other items to those who buy tobacco products.

g) Associating the brand name, logo, trademark, corporate emblem, or other identifiers of tobacco products with non-tobacco products or services (brand stretching) or implying a connection or association between non-tobacco products or services and tobacco products (brand sharing).

h) Sending direct messages or letters to individuals, engaging in telemarketing, conducting customer surveys or research, or using similar promotional methods.

i) Offering rewards or incentives to tobacco sellers, including providing bonuses or other forms of support to encourage sales of tobacco products.

j) Selling, offering, displaying, or openly showcasing tobacco products in educational institutions, health facilities, hospitality venues, sports facilities, entertainment venues, music and dance halls, social events, or similar places.

k) Selling or offering tobacco products disguised as toys, candies, or other similar products.

## Part Four:

## Miscellaneous Provisions

### 17. Administrative Measures

1) The authority shall take administrative action against any person who commits an offense by violating an obligation, responsibility, or requirement stipulated in this directive.

፪፡ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰደው የጥፋቱን ክብደት፣ የአፈጻጸሙን ሁኔታ እና ያደረሰውን ወይም ሊያደርስ ይችል የነበረውን የጉዳት መጠን በማገናዘብ ይሆናል።
፫፡ ፈቃድ ሲታገድም ሆነ ሲሰረዝ ባለስልጣኑ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት ያደርጋል።

**፲፰. ህገ-ወጥ የትምባሆ ምርት ንግድ**

፩፡ ማንኛውም ሰው የትምባሆ ምርትን በህገ-ወጥመንገድ ማምረት፣ ማከፋፈል፣ ማከማቸት፣ መሸጥ፣ በማንኛውም ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ገበያ ውስጥ ማስገባት አይችልም።
፪፡ አግባብ ያላቸው የመንግስት አካላት ህገ-ወጥ የትምባሆ ንግድን ጨምሮ የትምባሆ ምርት ዝውውርን በሚመለከት መረጃ የመያዝ እና የመከታተል ግዴታ አለባቸው።
፫፡ በአስተዳደሩ ዉስጥ በህገ-ወጥ መንገድ የተያዘ የትምባሆ ምርት ከተገኘ የአስተዳደሩ ባለስልጣን ምርቱን በመዉረስ እንዲወገድ ያደርጋል። እንደአስፈላጊነቱ የማስወገጃ ወጭዉን የምርቱ ባለቤት ይሸፍናል።
፬፡ አግባብ ያለቸው የመንግስት አካላት ህገ-ወጥ የትንባሆ ንግድን ለመቆጣጠር አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለባቸው።

**፲፱. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም የመተባበር ግዴታ አለበት።

**፳. ስለ ንግድ ሰንሰለት**

የትምባሆ ምርት አምራቾች የትምባሆ ምርትን የሚያቀርቡት አግባብ ካለው አካል የተሰጠ ህጋዊ ልዩ ፈቃድ ላላቸው ጅምላ አከፋፋዮች ብቻ ነው።

**፳፩. ስለ ትምባሆ ምርት አወጋገድ**

፩፡ ህገ-ወጥየሆኑ የትምባሆ ምርቶች፣ ማምረቻ መሳሪያዎችን እና ተያያዥ ምርቶች ሊወገዱ የሚችሉት የህብረተሰብ ጤናን በማይጎዳ ወይም አካባቢን በማይበክል መልኩ መሆን አለበት።
፪፡ የትምባሆ ምርት ማስወገድ የሚቻለው አግባብ ያለው አካል በማሳወቅ እና ተገቢውን መመሪያ ወይም ጋይድላይን መሰረት በማድረግ መሆን አለበት።

**፳፪. የአገልግሎት ክፍያ**

በዚህ መመሪያ መሰረት አገልግሎት የሚሰጠው ሰው ባለስልጣኑ በሚወስነው የክፍያ ተመን መሰረት የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፤

2) The administrative action to be taken shall be determined by taking into account the seriousness of the offense, the manner in which it was committed, and the extent of the damage caused or that could have been caused
3) Where a license is suspended or revoked, the authority shall notify the relevant concerned bodies accordingly.

**18. Illegal Trade of Tobacco Products**

1) No person may produce, distribute, store, sell, or introduce tobacco products into the market through illegal means.
2) Relevant government bodies are obligated to monitor and control the illegal trade of tobacco products, including the transfer of tobacco products.
3) If illegal tobacco products are found within the administration, the relevant authority will confiscate and dispose of them. The cost of disposal will be borne by the owner of the products.
4) Relevant government bodies must cooperate to control the illegal trade of tobacco products.

**19. Obligation to Cooperate**

Relevant federal and administrative government bodies, as well as private institutions and individuals, are obligated to cooperate in the implementation of this directive.

**20. Supply Chain**

Tobacco product manufacturers may only supply tobacco products to wholesalers who have obtained a valid special license from the relevant authority.

**21. Disposal of Tobacco Products**

1) Illegal tobacco products, manufacturing equipment, and related products must be disposed of in a manner that does not harm public health or the environment.
2) The disposal of tobacco products must be carried out by the relevant authority following proper notification and in accordance with appropriate guidelines or directives.

**22. Service Fees**

Any person providing a service pursuant to this directive shall pay a service fee in accordance with the tariff determined by the authority.

**፳፫. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም አሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚት አይኖረውም፡፡

**፳፬.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከ_____________ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ዶ/ር ፅጌረዳ ክፍሌ
የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ

**23. Invalid Provisions**

Any directive or procedural practice that contravenes this directive shall have no effect with respect to matters covered by this directive

**24. Effective Date**

This directive shall come into effect starting from ___________ (date) in the year 2026

Dr. Tsegereda Kifle
Dire Dawa Administration Health Bureau Head
Dire-Dawa

የትምባሆ ቸርቻሪ ልዩ ፈቃድ መስጫ ቅጽ

መለያ ቁጥር----------------------
ቀን-------------------------

- የችርቻሮ መደብሩ ንግድ ስም -----------------------
- የችርቻሮ መደብሩ ባለቤት ስም ----------------
- የችርቻሮ መደብሩ የግብር መለያ ቁጥር-------------
- መደብሩ የሚገኝበት አድራሻ--------ወረዳ--------

የቤ/ቁ---------

የትምባሆ ምርት የጤና፣የማህበራዊ፣የኢኮኖሚ እና አካባቢያዊ ችግር የሚያስከትል ከመሆኑም በላይ ትምባሆን መጠቀም እንደ ካንሰር፣ የመተንፈሻ አካል ህመም፣ የልብ እና የደም ስር የመሳሰሉትን በሽታዎች፣ የአካል ጉዳትን እንዲሁም ሞትን እንደሚያስከትል በሳይንስ የተረጋገጠ ነዉ። ለትምባሆ ጢስ መጋለጥ ትምባሆ በማያጨሱ ሰዎች ላይም ከፍተኛ የጤና ችግር፤ ሞት እና የአካል ጉዳት ስለሚያስከትል ይህንኑ መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም የፌደራል ምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 እንዲሁም የድሬዳዋ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 33/2015 የትምባሆ ምርትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የህግ ድንጋጌዎችን አካተዋል። በተጨማሪም የድሬዳዋ ምግብ፣ መድሃኒት እና ጤና ነክ ቁጥጥር ባለስልጣን የትምባሆ ምርትን ለመቆጣጠር ያወጣዉ መመሪያ ቁጥር----/2016 መሰረት የትምባሆ ምርትን ሽያጭ ለመቆጣጠር ለችርቻሮ ድርጅቶች ልዩ ፈቃድ መስጠት በማስፈለጉ፤ የልዩ ፈቃድ የሚወስዱ ቸርቻሪዎች በህግ የተጣለባቸዉን ግዴታ ማሟላት ይጠበቅባቸዋል። ስለሆነም የትመባሆ ምርት ለመቸርቸር ልዩ ፈቃድ የተሰጠኝ እኔ ------------------------ከታች የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ለመወጣት የተስማማሁ መሆኔን እየገለጽኩ እነዚህን ግዴታዎች ሳልወጣ ብቀር በህግ ተጠያቂነት ያለብኝ መሆኑን ተገንዝቤአለሁ።

1. እድሜአቸዉ ከ21 ዓመት በታች ለሆኑ ሰዎች መሸጥም ሆነ እንዲሸጡ ማድረግ በህግ የተከለከለ መሆኑን፤

2. የትምባሆ ምርቱን የምሸጥበት መደብር ከማናቸዉም የትምህርት፣ ጤና ተቋም እና ወጣት ማእከላት አካባቢ 100 ሜትር የራቀ መሆኑን

3. በፍሬ ወይም በነጠላ መሸጥ የሌለበኝ መሆኑን

4. የትምባሆ ምርቱ በመደብሬ ዉስጥ ለደንበኛ ሊታይ በሚችል ቦታ የማላስቀምጥ፤

5. የትምባሆ ምርት ማስታወቂያ ያለባቸዉም ማናቸዉም ቁሶች እንደ ፕላስቲክ፣ ጃንጥላ እና መሰል ቁሶች የማልጠቀም እና የማልሸጥ መሆኑን፤

**Special License Issuance Form for tobacco Retailers**

**Identification Number** ----------------------

**Date** -------------------------

**Name of the Retail Shop** -----------------------

- **Name of the Retail Shop Owner** ----------------
- **Tax Identification Number of the Retail Shop**
- **Address of the Shop** -------- **Woreda** -------- **House Number** ---------

tobacco products have been scientifically proven to cause health, social, economic, and environmental problems. In addition to these issues, the use of tobacco has been linked to serious health conditions such as cancer, respiratory diseases, heart and blood vessel-related illnesses, physical disabilities, and even death. Exposure to tobacco smoke also poses significant health risks, including death and physical harm, even to non-users, making its regulation essential.
Therefore, the Federal Food and Drug Administration Proclamation No. 1112/2011 and the Dire Dawa Administration Regulation No. 33/2015 include legal provisions to regulate tobacco products. Furthermore, based on Directive No. ----/2018 issued by the Dire Dawa Food, Drug, and Health Administration Authority to control tobacco production, special licenses are required for retail businesses to sell tobacco. Retailers who obtain this special license are expected to fulfill their legal obligations.
Accordingly, I, -----------------------, who have been granted a special license to retail tobacco, hereby declare my agreement to comply with the following obligations. I understand that failure to fulfill these obligations will hold me legally accountable.

1. **Prohibition of Sales to Minors**: It is prohibited by law to sell or facilitate the sale of tobacco to individuals under the age of 21.
2. **Location Restrictions**: The shop where I sell tobacco must be located at least 100 meters away from any educational institutions, health facilities, or youth centers.
3. **Prohibition of Bulk or Single Sales:** I am not allowed to sell tobacco in bulk or as single units.
4. **Display Restrictions:** I will not display tobacco products in a visible area of my shop accessible to customers.
5. **Advertising Restrictions:** I will not use or sell any items such as plastics, banners, or similar materials that advertise tobacco products.

6. ህጋዊ ያልሆኑ የትምባሆ ምርቶችን የማልሸጥ መሆኑን፤

7. ለተጠቃሚዎች የሲጋራ መለኮስ አገልግሎት የማልሰጥ መሆኑን፤

8. የችርቻሮ መደብሬ ፊት ለፊት ማጨስ የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ምልክት የማላስቀምጥ መሆኑን፤

ተገንዝቤ

ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የተስማማሁ መሆኑን በፊርማየ አረጋግጣለሁ::

| የችርቻሮ መደብሩ ባለቤት ወይም ወኪል ስም እና ፊርማ | ልዩ ፈቃዱን የሰጠዉ ስም እና ፊርማ |
|---|---|
| ------------------------------------ | ---------------------------------- |

6. **Prohibition of Illegal Products:** I will not sell any illegal tobacco products.
7. **No Smoking Services:** I will not provide cigarette lighting services to users.
8. **No Smoking Signage:** I will not place a "No Smoking" sign in front of my retail shop.

I acknowledge and confirm my commitment to implementing these obligations by signing below.

| **Name and signature of the Retail Shop Owner or Representative** | **Name and signature of the License Issuer** |
|---|---|
| -------------------------------------- | --------------------------------- |